# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን

# የ1996 ዓ.ም. የከተማ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ሁኔታ ጥናት የኤዲቲንግ እና ኮዲንግ መመሪያ

አዲስ አበባ
ጥቅምት 1996 ዓ.ም.

# የ1996 ዓ.ም. የከተማ ተከታታይ የሥራ ሥምሪት ጥናት
# የመጠይቅ ዕርማትና ኮድ አሰጣጥ መመሪያ
# /EDITING & CODING MANUAL

## ምዕራፍ 1

## መግቢያ

ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች የመረጃ ፋይዳ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም:: በመሆኑም መንግሥት በተለያየ ጊዜ ወቅታዊና ጥራት ያላቸውን መረጃዎች ቢቻል በሁሉም መልክ፣ መሰብሰብ ይህ ቀረው የማይባል ጥቅም ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል:: ከነዚህም የመረጃ ዓይነቶች መካከል የአንድ አገር የሰው ኃይል ብዛት በሥራ ዓይነትና በሥራ ዘርፉ፣በኢንዱስትሪ ወዘተ. መሰብሰብ በዘርፍ ለሚያስፈልገው መሻሻልና ክትትል ለፖሊሲ አውጭዎች አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል::

በዚህም መሠረት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን በጥቅምት ወር የከተማ ተከታታይ የሥራ ሥምሪት ጥናት በማድረግ መረጃ ሰብስቧል:: በዚህ ጥናት የተካተቱትም በከተማ ብቻ የሚገኙ የቆጠራ ቦታዎች እንደሆኑም ይታወቃል:: ጥናቱ ግቡን እንዲመታ አስተዋፅኦ ከሚያደርጉት ሥራዎች መካከል አንደኛው ከመስክ የሰበሰቡትን መረጃዎች በሚገባ አርሞና ኮድ ሰጥቶ ለሚቀጥለው የሥራ ክፍል ማስተላለፍ ነው:: ስለሆነም፣ የኮድ አሰጣጥና እርማት የማድረግ ተግባር በጥንቃቄ መከናወን ይኖርበታል:: በዚህ ጥናት የተካተቱ ጥያቄዎች አነስተኛ መሆንና የጥያቄዎቹ ዓይነት በመስክ ላይ ኮድ የሚደረጉ መሆናቸው በእርማቱና ኮድ አሠጣጡ ላይ ብዙ ጫና እንደማይፈጥር ይገመታል:: ይሁን እንጂ ጥያቄዎችን በቀላሉ እርስ በእርስ ለማመሳከር ይቻለው ዘንድ አራሚው ስለጥናቱ በቂ እውቀት ሊኖረው ይገባል:: ለምሳሌ :- የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ዓይነት መረጃ ኮድ ሲደረግ በመጠይቁ የተሞሉትን መረጃዎች በጥሞናና በእርጋታ ማየትና መረዳትን ይጠይቃል:: ስለሆነም፣ በመጠይቁ እርማትና ኮድ መስጠት ሥራ የሚሳተፉ ሠራተኞች የጥናቱን ውጤት በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ የሥራ ድርሻ የተጣለባቸው መሆኑን አውቀው የእርማትና ኮድ አሰጣጡን መመሪያ በደንብ መረዳት ይጠበቅባቸዋል::

ሀ. ኤዲቲንግ

ከልዩ ልዩ ጥናቶች የሚሰበሰቡትን መረጃዎት ኤዲት ማድረግ /ማረም/ የመረጃውን ጥራት ለመገምገምና እንደዚሁም ስህተቶችን፣ የሚቃረኑ መረጃዎችን፣ ሳይሞሉ የቀሩትን፣ ...ወዘተ በማረም የመረጃውን ጥራት ለማሻሻል ይረዳል::

ኤዲቲንግ ማለት የተሰበሰበውን መረጃ ሁኔታ በመመልከት በተሰጠው መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን እርማት ማድረግ ነው:: ኤዲተሩ /አራሚው/ ይህንን ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት የመረጃ መሰብሰቢያው ፎርም /መጠይቅ/ ለመረጃ ሰብሳቢው በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባዋል:: ኤዲተሩ /አራሚው/ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል::

1. ሳይሞሉ የቀሩ መረጃዎች

በመጠይቁ ሳይሞሉ የቀሩትን መረጃዎች በመፈለግ መመሪያውን በመከተል አስፈላጊውን እርማት ማድረግ ነው:: ሣይሞሉ በቀሩ መረጃዎች ፋንታ የሚሞላው መረጃ የሚገኘው ሌሎች የተሞሉ መረጃዎችን በማገናዘብና በመመርመር ነው:: በተቻለ መጠን ለተዘለሉና ሣይሞሉ ለቀሩ መረጃዎች በሙሉ አስፈላጊው እርማት ተደርጎ መሙላት የሚያስፈልግ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ሆኖም ሣይሞሉ ለቀሩት መረጃዎች በፎርሙ /መጠይቁ/ ከታዩት መረጃዎች አኳያ አመሳክሮና መርምሮ ለማረም የማይቻል ከሆነ በፈጠራ መሙላት ስለማይገባ ሣያርሙ ዓምዱን ባዶውን መተው ይመረጣል:: የዚህ ዓይነት ሁኔታ ኮድ ሲደረግ ላልታወቀ መልስ የሚሰጠው ኮድ ይበልጠዋል ማለት ነው::

2. ሊሆኑ የማይችሉና የማይመለሱ መልሶች

ሊሆኑ የማይችሉ መልሶችና የማይመለሱ መልሶችን በእርማት ጊዜ ማስወገድ ያስፈልጋል:: ሊሆኑ የሚችሉ መልሶች በመመሪያው ከተሰጠው ውጭ የተመለሱ መልሶች ሲሆኑ ለምሳሌ፣ ባለፈው ሳምንት ለስንት ቀናት ሠሩ? ለሚለው ጥያቄ በዓምዱ የሰፈረው ቀናት ብዛት ከ7 ቀን በላይ ከሆነ ይህ ሊሆን የማይችል መልስ በመሆኑ መታረም አለበት:: የማይመስሉ መልሶችን በተመለከተ የጋብቻ ሁኔታን እንደ ምሣሌ ብንወስድ የአንድ ሰው የጋብቻ ሁኔታ፣

1/ ፈጽሞ ያላገባ/ያላገባች

2/ ያገባ/ያገባች

3/ ባል/ሚስት የሞተባት

4/ የተፋታ/የተፋታች

ሲሆን ይህም መረጃ የሚሞላው እንደ ሁኔታው ለቤተሰብ አባላት በሙሉ ነው::

ስለዚህ ለአንድ ዕድሜው ሦስት ዓመት ለሆነ ህፃን የጋብቻ ሁኔታ "ሚስት የሞተችበት" ተብሎ ቢሞላ ዕድሜው አግብቶ ሚስቱ ልትሞትበት ስለማይችል መልስ ሊሆን የማይችል በመሆኑ መታረም አለበት::

3. *<u>የሚቃረኑ መልሶች</u>*

*የሚቃረኑ መልሶችንም ማረም ተገቢ ነው፡፡ የሚቃረኑ መልሶች የሚገኙት ከሁለት ወይም ከዚያ የበለጡ ሊዛመዱ የሚችሉ መልሶች ሳይዛመዱ ሲቀሩ ነው፡፡*

*<u>ለምሳሌ</u> ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ሥራ ሠርተዋል? ተብለው ለተጠየቁት መልስ "የለም" ብለው ኮድ "2" ለተሞላላቸው በሚቀጥለው ዓምድ የሥራ ሰዓት ተሞልቶ ከተገኘ የነዚህ ዓምዶች መልስ የሚቃረኑ መልሶች ናቸው፡፡ ይህም ማለት በሳምንት ውስጥ ምንም ሥራ ያልሰራን ሰው ስንት የሥራ ሰዓቶች ሠራህ ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያው ዓምድ ላይ የተሞላው ኮድ "2" የለም የሚለውን ስህተት ሊሆን ስለሚችል ተከታታይ ዓምዶችን መርምሮ ማየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ መልሶች ተመዝግበው ሲገኙ ከቀሩት ዓምዶች ጋር በማገናዘብ መረጃው ይታረማል፡፡*

4. *<u>ጽሁፉን ለማንበብ የሚያስቸግሩ መልሶች</u>*

*በትክክልና በደንብ የማይነበቡ መልሶችን ማረምና ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም እርማቱ በሚደረግበት ወቅት የሚፃፉ ጽሁፎች ሁሉ በደንብና በቀላሉ የሚነበቡ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡*

5. *<u>ከመመሪያ ውጭ ስለተሞሉ መልሶች</u>*

*በዚህ ጥናት ከመመሪያ ውጭ የተሞሉ መረጃዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የትምህርትና የጋብቻ ሁኔታ የሚጠየቀው ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ዕድሜው 9 ዓመት ለሆነው ህፃን የትምህርት ሁኔታ ተሞልቶለት ቢገኝ ምንም እንኳ ዕድሜያቸው 9 ዓመትና በታች የሆኑ ህፃናት በመደበኛ ትምህርት ቤት ገብተው መማር ቢችሉም መመሪያው ዕድሜያቸው 10 ዓመት እስካልሞላ ድረስ ስለትምህርት ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎች እንደማይጠበቅባቸው ስለሚገልጽ የተሞላው መረጃ ከመመሪያ ውጭ ስለሆነ መሠረዝ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የዓምዶችን ቅደም ተከተል ለማመልከት መረጃዎች ሲሞሉ ከየትኛው ዓምድ ወደ የትኛው ማለፍ እንደሚገባ በመጠይቁ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡*

*ስለሆነም መረጃዎች ይህንኑ ተከትለው መሞላት ስለሚገባቸው በመጠይቁ ላይ በተመለከተው መሠረት ያልተሞሉ መረጃዎች ከተገኙ መታረም ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ዓምድ 27 ኮድ 2 ከተሞላ እስከ ዓምድ 30 ያሉት ጥያቄዎች በሠረዝ መታለፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን ዓምድ 28 እና ዓምድ 29 ተሞልቶ ከተገኘ ዓምዶችን በማገናዘብ ማስተካከልና ማረም ያስፈልጋል፡፡ በመጠይቁና በመመሪያው ውስጥ በግልጽ እንደተመለከተው ለአሠራር ያመች ዘንድ መረጃዎች በኮድ ብቻ (ከጥቂት ዓምዶች በስተቀር) እንዲገለጽ ተደርጓል፡፡*

ሆኖም እያንዳንዱ መረጃ ሰብሳቢዎች በስህተት መልሶቹን በቃላትና በኮድ ሊመዘግቡ ይችላሉ:: ይህ አሠራር በተለይ መረጃዎች በኮምፒውተር በሚቀነባበሩበት ወቅት ችግር ስለሚፈጥሩ በቃላት የተመዘገቡትን መረጃዎች ከሚጣጣመው ኮድ ጋር ተገናዝቦ መሞላት ይገባዋል::

ለ. <u>ኮዲንግ</u>

ኮዲንግ ማለት በፎርሙ የተሰጡትን መልሶች ወደ አሀዝ መለወጥ ነው:: ይህም አሀዝ በቀላሉ መረጃውን በኮምፒውተር ለማቀነባበር ይረዳል:: የዕርማትና (Editing) የኮድ የማድረግ ተግባር በማጣመር ይካሄዳል:: በዚህ ፎርም የተሞሉት መረጃዎች በአብዛኛው አስቀድመው ኮድ ተደርገዋል:: ለምሳሌ ጾታ፣ ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ...ወዘተ ናቸው:: ለነዚህ መልሶች የዕርማት ተግባር ለማከናወን ኮዶቹ በመመሪያው መሠረት መሞላታቸውን ማረጋገጥ ብቻ ነው:: እንደ አዲስ ኮድ መደረግ ያለባቸው መልሶች ደግሞ በክፍል 1 የተገለፁት የአካባቢ መለያ መልሶች ናቸው:: እነዚህን መልሶች ኮድ ለማድረግ የሚረዱ የኮድ ዝርዝር ይሰጣል:: ይህ የኤዲቲንግ ኮዲንግ መመሪያም የአሠራሩን ሁኔታና ዘዴ የሚገልጽ ጽሁፍ ነው::

# ምዕራፍ II

## አጠቃላይ መመሪያ

1. የእርማቱና ኮድ አሰጣጡ ሥራ መከናወን ያለበት ለዚሁ በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት መሆን እንዳለበት ማስታወስ ይገባል፡፡ አንዳንድ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተጠቀሱ ነገሮች ሲያጋጥሙ ጥያቄዎቹን ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማቅረብ መፍትሔ እንዲሰጠው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

2. ሥራውን ለማከናወን መነሻው በመስክ የተሞላው መረጃ ስለሆነ አስቀድሞ እያንዳንዱ መጠይቅ መሞላቱንና ተሟልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በአንድ ቆጠራ ቦታ ለ30 ቤተሰቦች መረጃ ተሞልቶአል፡፡ ለእያንዳንዱ ቤተሰብም አንድ ባለ 3 ገጽ /A3 Size/ መጠይቅ የተሞላ ሲሆን፣ ተጨማሪ መጠይቅም ተሞልቶላቸው ከሆነ ሁለት ባለ 3 ገጽ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ አንዳንድ በመረጃው አሰባሰብ ጊዜ ያጋጠሙትን ሁኔታዎች የሚያብራሩና ከመጠይቁ ጋር ተያይዘው የመጡ አስተያየቶችን በሚገባ መያዛቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

3. እርማት በሚደረግበትና ኮድ በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ሥራው ከሚመለከተው ኃላፊ ካልታዘዘ በስተቀር ማንኛውም በመረጃ ሰብሳቢው የሰፈረው ነገር መፋቅ/መጥፋት የለበትም፡፡ መረጃውን እርማት የሚያደርግበት ከሆነ ካሰፈረው መረጃ አጠገብ መረጃው ከተፃፈበት ቀለም በተለየ ቀለም እርማቱ ይደረጋል፡፡

# ምዕራፍ III

## መጠይቁን ማረም

**ክፍል 1** *የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ*

*ከዓምድ1 እስከ 8 ያለውን የክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ከፍተኛ/ወረዳ/ክፍለ ከተማ፣ቀበሌ ስሞች እና የቆጠራ ቦታ በትክክል መሰጠቱን ለማገናዘብ ማስተካከል ያስፈልጋል:: እንዲሁም ከክልል እስከ ቀበሌ ላሉት ዓምዶች ካርድ ኮለሞቹ መስክ ላይ ያልተሞሉ ስለሆነ፣ በእዝል የቀረበውን የአካባቢ መለያ ኮድ በመጠቀም ካርድ ኮለሞቹን መሙላት ያስፈልጋል::*

*ዓምድ 1-3 :-* **ክልል፣ዞን፣ወረዳ:-** *ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል፣ዞንና ወረዳ ስም በዓምዱ በተሰጠው ቦታ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ አለበት:: በካርድ ኮለሞቹ ተስማሚው ኮድ ይሞላል::*

*ዓምድ 4 : -* **ከተማ: -** *ከከተማው ጥናት የተመረጠው የከተማ ስም በተሰጠው ቦታ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ኮዱ ደግሞ በካርድ ኮለሞች ይሞላል::*

*ዓምድ 5: -* **ከፍተኛ/ ወረዳ/ክፍለ ከተማ: -** *ጥናቱ በከተማ የተካሄደ ስለሆነ የከፍተኛው ስም በአዲስ አበባ ደግሞ የክፍለ ከተማው ስም ፣በዓምዱ በተሰጠው ቦታ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::*

*ዓምድ 6: -* **ቀበሌ: -** *በከተማው ውስጥ ቀበሌው የሚጠራበት ስም በተሰጠው ቦታ መሞላቱን ማረጋገጥ እና በካርድ ኮለሞቹ ደግሞ የቀበሌው ኮድ በትክክል መሞላቱ ይረጋገጣል::*

*ዓምድ 7: -* **የቆጠራ ቦታ:-** *የቆጠራ ቦታ ኮድ በካርድ ኮለሞቹ በትክክል መሞላቱን ማጤን ያስፈልጋል::*

*ዓምድ 8: -* **የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር:-** *በአንድ የቆጠራ ቦታ በጥናቱ የሚመረጡ ቤተሰቦች በጠቅላላ ብዛት 30 ነው:: ስለሆነም በዚህ ዓምዱ ባሉት በካርድ ኮለም የተሞሉ ቁጥር ከ01-30 መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::*

*ዓምድ 8ሀ: -* **የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም : -** *በዚህ ዓምድ የቤተሰቡ ኃላፊ ሙሉ ስም መፃፉን እንዲሁም በክፍል 2 ዓምድ 11 በመጀመሪያ ተራ ቁጥር ላይ መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ይህ ባይሆን ግን ከተቆጣጣሪው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ማስተካከል ያስፈልጋል::*

*ማሳሰቢያ፣* *በእያንዳንዱ መጠይቅ በቀኝ አናት ላይ የቀጠለ መጠይቅ አለ በሚለው አንፃር የተደረገውን ምልክት መሠረት በማድረግ የቀጠለ መኖሩንና አለመኖሩን ማጣራትና ተገቢውን እርማት ማድረግ ተገቢ ነው::*

*<u>ዓምድ 9ሀ</u>:-* **<u>ቅ/ጽ/ቤት</u>**

በዚህ ዓምድ የቅ/ጽ/ቤቱ ሥም በዓምዱ በተሰጠው ቦታ ተሞልቶ ለቅ/ጽ/ቤቱ የተሰጠው መለያ ኮድ ደግሞ ከዓምዱ ሥር ባሉት ሁለት ካርድ ኮለሞች መሞላታቸው ይረጋገጣል::

*<u>ዓምድ 9ለ</u>:-* <u>የቆጠራ ቦታ ተከታታይ ተራ ቁጥር</u>

በዚህ ዓምድ ስር ባሉት ሁለት ካርድ ኮለሞች ለቆጠራ ቦታው የተሰጠው መለያ ተከታታይ ቁጥር በቆጠራ ቦታው ለተሞሉት መጠይቆች በሙሉ የተለየና ለሌላ ቆጠራ ቦታ ያልተሰጠ ብቸኛ መለያ ቁጥር መሞላቱ ይረጋገጣል::

*<u>ዓምድ 9ሐ</u>:-* <u>የቀጠለ መጠይቅ አለ?</u>

ከተሞላው መጠይቅ በተጨማሪ የቀጠለ ወይም የተጨመረ መጠይቅ መኖሩንና አለመኖሩን የሚረጋገጥበት ስለሆነ መጠይቁ ታርሞ ከማለቁ በፊት በጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል::

## ክፍል 2:- <u>ስለቤተሰብ አባላት ዝርዝር መረጃ</u>

ከዓምድ 10-14 <u>ለሁሉም የቤተሰብ አባላት የሚጠየቁ ጥያቄዎች</u>

*<u>ዓምድ 10</u>:-* <u>ተራ ቁጥር</u>:- ይህ ከ01 በመጀመር በተከታታይ ቁጥር የተሰጠበት ስለሆነ ምንም አይነካም:: ሆኖም የቤተሰቡ አባላት ከ11 በላይ ባለመሆናቸው በተጨማሪነት ጥቅም ላይ የዋለ መጠይቅ መሆኑ ከተረጋገጠ ወይም በእያንዳንዱ መጠይቅ የቀኝ አናት ላይ የቀጠለ መጠይቅ አለ በሚለው አንፃር የተደረገውን ምልክት መሠረት በማድረግ ከታወቀ እና ተራ ቁጥሮቹ በመስክ ላይ ካልተስተካከሉ አራሚው በተጨማሪው መጠይቅ ላይ "01" ወደ "12"፣ "02" ወደ "13" በመቀየር ማረም ይኖርበታል:: 12 አባላት ላሉት ቤተሰብ የ12ኛው አባል መረጃ ሌላ መጠይቅ ሳያስፈልግ እዛው መጠይቅ ግርጌ ከ11ኛው አባል በመቀጠል ሊሞላ ስለሚችል አራሚዎች በሥራቸው ወቅት ይህን ማስተዋል አለባቸው::

*<u>ዓምድ 11</u>: -* <u>የቤተሰብ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም</u>: - የቤተሰቡ አባላት ስም የሰፈረበት ዓምድ ስለሆነ ምንም ዓይነት እርማት አይደረግበትም::

*<u>ዓምድ 12</u>: -* <u>ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና:-</u> በዚህ ዓምድ ስር ባለው ንዑስ ዓምድ መረጃ ሰብሳቢው መሙላት ያለበት የኮድ ቁጥሮች ከ01-09 ያሉትን ብቻ ነው:: አባላቱ ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸውን ዝምድና የሚገልፅበት ኮዶች እና የሰጠው መግለጫና ኮድ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ እና የማይዛመድ ከሆነ ኮዱን ማስተካከል ያስፈልጋል:: የኮዶቹ ዝርዝርና መግለጫቸው ከጥያቄው ሥር ይገኛል::

*<u>ዓምድ 13</u>: -* <u>ጾታ:-</u> በዚህ ዓምድ ባለው ክፍት ቦታ መታየት ያለባቸው 1 ወይም 2 ብቻ ናቸው:: ስለ ኮዱ ትክክለኛነት በዓምዱ ሥር በተሰጠው ቦታ የሰፈረውን የፆታ መለያ ማየት ያስፈልጋል:: ሆኖም መረጃ ሰብሳቢው በስህተት ኮድ

ሳይሰጥ ቢቀር ተቆጣጣሪውን በማማከር የግለሰቡን ፆታ ከልዩ ልዩ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ መሞላት ይኖርበታል:: ፆታ ካልተገፈ ስም ታይቶ ይሞላል:: ይህም ካልተቻለ መጠይቁ ወደተሰበሰበበት ቅርንጫፉ ስልክ በመደወል በማጣራት ይሞላል:: ከዚህ ሁሉ ሙከራ በኋላ ግን ይሆናል ተብሎ የሚገመተው በግምት ይሞላል እንጂ ኮድ 9 መሙላት አይፈቀድም::

<u>ዓምድ 14</u>: - <u>ዕድሜ</u>:- ይህ ዓምድ የቤተሰቡ አባላት ተጠይቀው ተሞልቶ የመጣ ነው:: ሆኖም በዚህ ዓምድ ባሉት ንዑስ ዓምዶች ከ97 በላይ ቁጥር መታየት የለበትም ከ97 በላይ የሆነ ቁጥር ከታየ "97" ተብሎ መስተካከል ይኖርበታል:: ዕድሜ ካልተገፈ ዝምድናና የልጆች ዕድሜ ፣የባል/የሚስት ዕድሜ ታይቶ በተቀራራቢ እሳቤ/ግምት/ ይሞላል:: በተጨማሪም የዕድሜ መረጃ ካልተሞላ የቤተሰብ አመዘጋገብ ቅደም ተከተልና በዕድሜ ከተሞሉ ዓምዶች ለግለሰቡ የተሞሉ መረጃዎችን በማመሳከር መረጃዎችን ለመሙላት ይሞከር:: ይኸውም ሲሆን፣ ከተቆጣጣሪው ጋር በመመካከር የሚፈፀም ይሆናል:: እንጂ ኮድ 99 መሞላት የለበትም::

<u>ዓምድ 15-16</u> :- <u>የትምህርት ሁኔታ /ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ/</u>

<u>ዓምድ 15:-</u> <u>ማንበብና መፃፍ ይችላሉ?</u>

ይህ ዓምድ 10 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰቡ አባላት ማንበብና መፃፍ መቻላቸው ተጠይቆ "አዎን" ለመለሱ ኮድ 1 "የለም" ብለው ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 የተሞላበት ነው::ስለዚህ በካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልተው የሚመጡ ቁጥሮች ከ "1" ወይም ከ "2" ውጭ መሆን የለባቸውም:: ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ በሚቀጥለው ዓምድ /ዓምድ 16/ ላይ ከተሞላው መረጃ ጋር ማስተካከል እንደሚቻል መረዳት ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 16</u>- <u>የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ስንተኛ ነው?</u>

የመጣው መረጃ በአሮጌው /በድሮው/ እና በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ተለይቶ ምላሾችና ኮዶች ተጣጥመው የተሞሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: ይህም ማለት የጨረሰው ክፍል በአዲሱ ተብሎ ከአሮጌው ኮድ ተሞልቶ ቢገኝ በጽሁፉ መሠረት በአዲሱ ስርዓት ኮድ መሠረት ተለውጦ መስተካከል ይኖርበታል:: <u>ምሳሌ</u> 6ኛ በአዲሱ ቢባል ሊፃፍ የሚገባው ኮድ "36" ይሆናል ማለት ነው::

<u>ዓምድ 17</u>:- <u>የቴክኒክ ሥልጠና ወስደው ያውቃሉ? ወረቀት ወይም ከዚያ በላይ ማስረጃ ላላቸው ::</u>

በዚህ ዓምድ ለሚገኘው ካርድ ኮለም አዎን ለመለሱ ኮድ 1፣ የለም ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም በዚህ ዓምድ የለም መልሰው ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም በዚህ ዓምድ የለም መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው የሚቀጥሉት ዓምዶች ማለትም ዓምድ 18 እና 19 ሳይሞላላቸው በሰረዝ ታልፈው ወደ ዓምድ 20 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ በዓምድ 18 ላይ ከተሞላው መረጃ ጋር በማገናዘብ መሙላት ያስፈልጋል::

ዓምድ 18:- የሰለጠኑበት የሙያ /ቴክኒክ ሥልጠና/ ዓይነት ምንድን ነው?

በዓምድ 17 የሙያ /ቮኬሽናል/ቴክኒካል/ ሥልጠና ወስጄና አጠናቅቄ የምስክር ወረቀት ወይም ከዚያ በላይ አግኝቼአለሁ ብለው መልሰው ኮድ 1 የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ የሰለጠኑበት የሙያ (ቮኬናል/ቴክኒክ) ዓይነትና ተገቢው ኮድ በካርድ ኮለሙ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የሙያ አይነቶችንና ተገቢው ኮድ በካርድ ኮለሙ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የሙያ አይነቶችን ከተገቢው ኮድ ጋር ለማገናዘብ ከታች የቀረበውን ዝርዝር ይመልከቱ:: /ዝርዝሩ ተወስዶ መፃፍ ይኖርበታል/

| | | | |
|---|---|---|---|
| | (ሀ) ፕሮፌሽናልና፣ መለስተኛ ፕሮፌሽናል፣ | 38 | ባዮሎጂ (ስነሕይወት) |
| 01 | ግብርና ሳይንስ<br>እርሻ ኢኮኖሚክስ፣እርሻ ምህንድስና፣እርሻ ኤክስቴንሽን ፣ የእንሰሳት ሳይን የስኬል ጥበቃ፣ አጠቃላይ እርሻ፣የደረቅ አካባቢ እፅዋትየእንሰሳት፣ ግጦሽ ሳይንስ፣ ፖስት ሃርቨስት ቴክኖሎጃ፣ የእንሰሳት ፕሮዳክሽንና | | |
| 02 | ውሀና አፈር ጥበቃ፣ | 39 | ኬሚስትሪ |
| 03 | ደን ሳይንስ፣ | 40 | ጂኦሎጂ |
| 04 | አጠቃላይ ሕክምና<br>አፐቶሞሎጂ፣ፓቶሎጂ፣ኢንተርሽናል ሜድስን ፣ጋይናኮሎጂ፣ሰርጀሪ ፣ኢንስቲቲዮሎጂ፣ | 41 | ፊዚክስ |
| 05 | ሜዲካል ላብራቶሪ/ራዲዮሎጂ/ | 42 | ማቲማቲክስ |
| 06 | ፋርማሲ/ፋርማሲ ቴክኒሽያን/ | 43 | ስታቲስቲክስ |
| 07 | ሳኒተር ሳይንስ | 44 | ዲሞግራፊ |
| 08 | ክሊኒካል ሳይንስ/ነርሲንግ | 45 | የኮምፒውተር ሳይንስ/ኢንፎርሜሽን ሳይንስ |
| 09 | ፓብሊክ ሄልዝ ነርስ ጤና መኮንን፣የአካባበ ጤና ፣ ፓስት ሄልዝ ኦፊሰር | 46 | ጤናና የአካል ማሰልጠኛ ትምህርት |
| | | | (ለ) የሙያና ቴክኒክ፣ |
| 10 | ጥርሶኔልና ቢዝነስ ማኔጅመንት | 47 | የባልትና ሳይንስ |
| 11 | ኢኮኖሚክስ | 48 | የቆዳ ሥራዎች ሥልጠና |
| 12 | ሂሣብ አያያዝ /ACCOUNTING/ | 49 | የውበት ሥራዎች ሥልጠና |
| 13 | ሴክሬቴሪያል ሳይንስ | 50 | የቪድዮ ፎቶግራፍ ቀረጻ ሥልጠና |
| 14 | ባንክና ፋይናንስ | 51 | ሸክላ ስራ |
| 15 | ሕግ | 52 | ሀመና |
| 16 | ስነጽሑፍና ቋንቋ የኢትዮጵያ የውጭ ቋንቋዎች ስነፅሑፍ/ | 53 | እንጨት ሥራ /የአናጢነት ስልጠናን ይጨምራል/ |
| 17 | ሥነኪነት | 54 | ኤሌክትሪክ ሥራ |
| 18 | ኢዱኬሽን ፔዳጎጂ<br>መምህርነት፣ካሪኩለም ኢንስትራክሽን፣ ኢዱኬሽን አድሚኒስትሬሽን ፣ የጐልማሶች ትምህርት | 55 | ብረታ ብረት ብየዳና ቅጥቀጣ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 19 | ጂኦግራፊ | 56 | መካኒክ /የመኪና/ የሞተር ሳይክል/ የአውሮፐላን ጥገናን ይጨምራል/ |
| 20 | ታሪክ | 57 | ግንበኝነት |
| 21 | ፖለቲካል ሳይንስ | 58 | ታይፕ |
| 22 | ሶሲዮሎጂዎና አንትፖሎጂ | 59 | ልብስ ስፌት |
| 23 | ስነልቦና /ሳይኮሎጂ/ | 60 | ሹፌርነት |
| 24 | ሲቪል መሃንዲስ/ህንፃ መሃንዲስ/ | 61 | የልማት ተጠሪ /DA/ |
| 25 | መካኒካል መሃንዲስ | 62 | ልምድ አዋላጅ |
| 26 | ኤሌክትሪካል መሃንዲስ | 63 | ኮምፒውተር አጠቃቀም |
| 27 | ኢንዱስትሪያል ምህንድስና | 64 | በግብርና አነስተኛ ስልጠና ሙያ /ከአጋርፋ፣ አርዳይታ፣ ባኮ፣ |
| 28 | የማዘጋጃ ቤት ምህንድስና/አርክቴክቸር | 65 | ሆቴልና ቱሪዝም |
| 29 | ለሎች ምህንድስናዎች ድራይላንድ ባዮዲይቨርስቲ፣ ሃይድሮሊክስ ፣ የመስኖ ምህንድስና | 66 | ፖሊስ |
| 30 | አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ | 67 | ውትድርና |
| 31 | ኮንስተራክሽን ቴክኖሎጂ | 68 | ሌላ ፕሮፌሽናልና፣ መለስተኛ ፕሮፌሽናል /ይገለጽ/ |
| 32 | ድራፍቲንግ ቴክኖሎጂ | 69 | ሌላ የሙያና ቴክኒከል /ይገለጽ/ |
| 33 | ማኒፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ | | |
| 34 | የብረታ ብረት ቴክኖሎጂ | | |
| 35 | የእንስሳት ጤና አጠባበቅ (የከብት ሕክምና/ | | |
| 36 | ኮሙኒኬሽን | | |
| 37 | ፓወርና የመሳሰሉት ኢንስትሩመንቴሽን ፣ ኤሌክትሪካል ፓወር፣ ሜካኒካል ፓወር፣ ማኒፋክቸሪንግ ፓወር፣ | | |

ዓምድ 17-19 የሥልጠና ሁኔታ፣ ( *ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ*)

ዓምድ 19:- *ሥራዎን የሚሽሩት በሠለጠኑበት ሙያ መስክ እየሰሩ ነው ? ካልሠሩ አንድ ዋና ምክንያት ?*

*በዚህ ዓምድ ግለሰቦች የሙያ ስልጠና ወስደውና በዓምድ 17 " አዎን" ብለው የመለሱ ሲሆን፣ በዚህ ጥያቄ ደግሞ ቢያንስ ካሁን በፊት በሰለጠኑበት ለማናቸውም ሙያ አሁን እየሰሩ እንደሆነና እንዳልሆነ ተጠይቀዋል:: ስለሆነም እየሰሩ ካልሆነ ኮድ "00" ተሞልቶ "እየሰራሁ" የሚል ደግሞ መፃፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በሌላ ሁኔታ ላይ ደግሞ ከተሰጡት አማራጭ ኮዶች ተገቢው ኮድ መሞላቱንና ይህም ከ01-11 ባለው ውስጥ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል::*

ዓምድ 20:- *የጋብቻ ሁኔታ:-*

ይህ ዓምድ የሚሞላው ዕድሜያቸወ 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ ስለሆነ ከ10 ዓመት በታች ለሆኑ ግለሰቦች ሳይሞላ መምጣቱን በስህተት ተሞልቶም ከመጣ ከተቆጣጣሪው ጋር በመመካከር መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል:: በአንፃሩም ከ10 ዓመት በላይ ለሆነው ግለሰብ መረጃ ተሞልቶ መምጣት ሲገባው ሳይሞላ ከመጣ አስፈላጊውን እርምት/ማገናዘብ በማድረግ ኮድ መሞላት ይኖርበታል:: በተጨማሪም በካርድ ኮለም ውስጥ ተሞልተው የመጡ ቁጥሮች ከኮድ 1-5 ከተዘረዘሩት ውጭ እንዳልሆነ ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

## ክፍል 3:- ያለፉት 6 ወራት የሥራ ሁኔታ

## /ከዓምድ 21-26 ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ/

ዓምድ 21:- **ባለፉት 6 ወራት ለጥቂት ጊዜም እንኳን ቢሆን በምርታማ ሥራ ማለትም ተቀጥረው ወይም ትርፍ ለማግኘት ወይም ለቤተሰብዎ ገቢ በሚየስገኝ ሥራ ተሰማርተው ነበር ?**

ለዚህ ጥያቄ እንደ አማራጭ የተሰጡት መልሶች "አዎን" እና "የለም" ሲሆኑ በዚህ መሠረት በዓምድ ስር "አዎን" የሚለው ቃል ከተፃፈ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 መፃፉን ማገናዘብ ያስፈልጋል:: ይህ ሁሉ ከተረጋገጠ በኋላ "አዎ" ብለው ኮድ 1 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 23 መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል::

ዓምድ 22:- **ባለፉት 6 ወራት ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ሥራ ለማግኘት /ለመሥራት ዝግጁ ነበሩ ?**

በዚህ ጥያቄ መልስ ሰጪዎች በዓምድ 21 ኮድ "2" የተሞላላቸው ሲሆን፣ ይህን ዓምድ ደግሞ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱን ማለትም አዎን ኮድ "1" ወይም የለም ኮድ "2" ሊሞላላቸው ይገባል:: የለም ብለው

መልሰው ኮድ "2" የተሞላላቸው ቀጣይ ዓምዶችን /ከ23-25/ ሳይሞላ ወደ ዓምድ 26 መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 23:- በ ----- ወር ለምን ያህል ሳምንታት በምርታማ ሥራ ላይ ተሰማርተው ነበር ወይም ደግሞ ለምን ያህል ሳምንት ሥራ አጥ ነበሩ ?

ይህ ጥያቄ ተጠያቂዎች ባለፉት 6 ወራት ምን ያህል ሳምንታት በሥራ ላይ ምን ያህል ደግሞ ሥራ አጥ እንደነበሩ ለማወቅ በወራት ተከፋፍሎ ተጠይቋል፡፡ በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ በዓምድ /Column/ የወር ስም የተፃፈ ሲሆን፣ የሥራ ሁኔታ ተብሎ "ሥራ ላይ" እና "ሥራ አጥ" ተብሎ አግድም/Row/ ተሠጥቷል፡፡ ስለሆነም በእያንዳንዱ ወር አንፃር "ሥራ ላይ" የሚለው እና "ሥራ አጥ" የሚለው ድምር ቢበዛ ከ4 መብለጥ አይኖርበትም፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታም ሥራ ላይ ለሚለው ትይዩ የተሞሉት የሳምንታት ብዛት ድምር በሚለው አቅጣጫ ሲታይ ከ24 መብለጥ የለበትም፡፡ በመጨረሻም ጠቅላላ ድምር/ጠ/ድምር/ በሚለው አንፃር ሊሞላ የሚችለው ትልቁ ቁጥርም 24 ስለሆነ የተሞላው ከዚህ ያልበለጠ መሆኑን ማስተዋል ይገባል፡፡

ዓምድ 24:- ሥራ ሳይኖርዎት ቆይተው ባለፉት 6 ወራት የጀመሩት ሥራ ነበርን?

ይህ ዓምድ ከላይ ጥያቄ/በዓምድ 23 የተጠየቁትን በሙሉ የሚያስተናግድ ሲሆን፣ መጠየቅ የማይገባቸው ደግሞ አለመጠየቃቸውን ማጣራት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ጥያቄ ኮድ "2" ኮድ "1" አዎን የሚሉ የለም አማራጮች የተሰጠ ሲሆን፣ መረጃ ሰብሳቢው ከተሰጡት ኮዶች ውጭ አለመመላቱን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

ዓምድ 25:- ባለፉት 6 ወራት ሥራ ላይ /ሥራ አጥ የነበሩበት አጠቃላይ የሳምንታት ድምር ፣

በዓምድ 23 የመጨረሻው ንዑስ ዓምድ ማለትም ጠ/ድ የሚለውን በማየት የተሞላ ሲሆን ይህም የማጣሪያ ዓምድ ነው፡፡ ይህም ማለት በዓምድ 23 ጠ/ድ በሚለው አንፃር 13 ሳምንታት በታች የተሞላ ከሆነ በዚህ ዓምድ ኮድ 1 የሚሞላለት ሲሆን፣ ከ13 ሳምንታት እና በላይ ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ተሞልቷል፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ከሆነ ግን በተሰጠው መመሪያ መሠረት ይስተካከላል፡፡ በተጨማሪም በዚህ የማጣሪያ ጥያቄ ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ 26 ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 27 መሸጋገራቸውን ማጣራት ያሻል፡፡

ዓምድ 26:- ባለፉት 6 ወራት ከ13 ሳምንታት በላይ ሥራ ያልሰሩበት ወይም/ሥራ ለመስራት ዝግጁ አልነበሩም? ያልነበሩበት ምክንያት ምን ነበር?

ይህ ዓምድ ለመልስ ሰጪዎች ስራ ያልሰሩበትን ምክንያት ከተሰጡት አማራጮች ከ0-8 የመለሱ ሲሆን ከነዚህ ቁጥሮች/ኮዶች/ ውጭ ሌላ ከተሞላ መስተካከል ያስፈልገዋል፡፡ በመሆኑም ሥራ ያልሠሩበት ዋነኛ ምክንያት በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ ተገልጾ በተጨማሪም በዓምድ 22 የለም ብለው ኮድ "2" የተሞላላቸው ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠታቸው ይረጋገጣል፡፡ ተገቢው ኮድ ደግሞ ከስር ባለው ካርድ ኮለም ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

## ክፍል 4 - ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሁኔታ

ከዓምድ 27 - 43 (ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ)

ዓምድ 27:- ባለፉት 7 ቀናት ለጥቂት ጊዜም እንኳን ቢሆን በምርታማ ሥራ ማለትም ተቀጥረው በክፍያ ወይም ትርፍ ለማግኘት ወይም ለቤተሰብዎ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተው ነበር ?

ይህ ጥያቄ ከዚህ በኋላ ለሚመጡ ዓምዶች መነሻና መሠረታዊ ጥያቄ ስለሆነ በጥንቃቄ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ስለሆነም በቅፅ (በመጠይቁ) ላይ ከተዘረዘሩት ምርታማ ሥራዎች ቢያንስ በአንዱ ለተሰማራ የቤተሰብ አባል "አዎን" የሚለው ኮድ 1 መሞላቱን በአንፃሩም በአንዱም እንኳን ላልተሰማራ "የለም" የሚለው ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ስለዚህ በካርድ ኮለሞቹ ውስጥ መታየት የሚገባቸው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ብቻ መሆን አለባቸው:: በተጨማሪም "የለም" መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው የሚቀጥሉትን ሁለት ዓምዶች (28 እና 29)ን ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 30 መሻገራቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው::

*ማሳሰቢያ:- በዚህ ዓምድ ምርታማ ሥራ ሠርተው ኮድ "1" የተሞላላቸው በዓምድ 21 ሞለፉት 6 ወራት ለጥቂት ጊዜም እንኳ በመሥራታቸው ኮድ 1 መሞላት ይኖርበታል:: በተለየ ሁኔታ ተሞልቶ ከመጣ ግን ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ተመልሶ ማረምና ማስተካከል ያስፈልጋል::*

ዓምድ 28:- የምሣና የጉዞ ሰዓትን ሳይጨምር ባለፉት 7 ቀናት በሠሯቸው በሁሉም ሥራዎች ለስንት ሠዓት ሰርተዋል? / የትርፍ ሰዓትንም ሥራ ያጠቃልላል/

በዚህ ዓምድ ባለፉት 7 ቀናት በጠቅላላው የተሰራ የሥራ ሰዓት መጠን መመዝገቢያ ነው:: እንደ ዓምድ 27 ሁሉ ይህም ዓምድ መሠረታዊነት ያለውና የቤተሰብ አባላትን ሥራ እያላቸው፣ ሥራ አጥ ለመባል ወይም ከሁለቱም ውጭ የሆኑትን ለመለየት ስለሚረዳን ነው:: ስለዚህ በዚህ ዓምድ ያሉት መረጃዎች በጥንቃቄ መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የሳምንት የሥራ ሰዓትም ድምር "97" እና ከዛ በላይ ከሆነ "የሳምንቱ ድምር" በሚለው ንዑስ ዓምድ ሥር መታየት ያለበት ቁጥር "97" ብቻ ነው:: በተለየ መልክ

ተሞልቶ ከተገኘ በዓምዱ ማረምና ማስተካከል ያስፈልጋል:: በተቻለ መጠን በነዚህ ዓምዶች ኮድ 99 አለመሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 29:- በዓምድ 27 ባለፉት ሰባት ቀናት የሰሩት የስራ ሰዓት ድምር

ለዚህ ጥያቄ የቀረቡት ሁለት አማራጭ መልሶች ሲሆኑ እነሱም ኮድ 1-4 ሰዓትና በላይ ሲሆን ኮድ 2 ደግሞ ከ4 ሰዓት በታች የሚሉ ናቸው:: በመሠረቱ ይህ ዓምድ መረጃ ስለጎደለው መልስ ሰጪዎችን ሳይጠይቅ ዓምድ 28 ላይ የተሞላውን የስራ ሰዓት ድምር በማየት የሚያጣራበት ስለሆነ ማጣራቱ በትክክል መካሄዱን ዓምዱ ላይ ከተሞላው ጋር ማገናዘብ ያሻል:: በተጨማሪም ለዚህ ዓምድ ኮድ 1 የተሞላላቸው ብቻ ቀጣዩን ዓምድ ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 31 መሸጋገራቸው መረጋገጥ ይኖርበታል::

ዓምድ 30:- ሥራ እያለዎት ነበር ባለፉት 7 ቀናት በሥራ ላይ ያልተሰማሩት?

በዚህ ዓምድ መረጃ ተሞልቶ የሚመጣው በዓምድ 27 ኮድ 2 ለተሞላላቸውና በዓምድ 29 ደግሞ ከ4 ሰዓት በታች ሠርተው እንዲሁ ኮድ 2 ለተመዘገበላቸው ነው:: ስለዚህ ከ4 ሰዓት በታች ለሠሩ የቤተሰብ አባላት ሥራ እያላቸው ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በሥራ ላይ ካልተሰማሩ አዎን የሚለው ኮድ "1-3" ሲሞላ ነገር ግን ሥራ ሳይኖራቸው ከሆነ የለም የሚለው ኮድ "4" ሊሞላላቸው ይገባል:: በመጨረሻም በዚህ ዓምድ የለም በሚለው ኮድ "4" የተሞላላቸው ግለሰቦች እስከ ዓምድ 42 ድረስ ምንም መረጃ ሳይሞላላቸው በሰረዝ "-" ታልፈው በቀጥታ ወደ ዓምድ 43 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

ዓምድ 31:- የዋነኛ ሥራዎ ዓይነት ምንድን ነው?

በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸወ ነገር ግን በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ያልነበሩ ግለሰቦች (በዓምድ 30 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው) በዚህ ዓምድ የዋነኛ ሥራቸወ ዓይነት ተሞልቶ መጥቷል:: ለዚህ ዋነኛ የሥራ ዓይነት ተገቢ የሆነው የመለያ ኮድ "የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምደባና ኮድ ዝርዝር" ተብሎ ከተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ይሞላል:: በካርድ ኮለሞቹ ኮድ ከመሞላቱ በፊት የተሞላውን የሥራ ዓይነት በደንብ ማጤን ይገባል:: የዋነኛ የሥራ ዓይነቱን ከኮድ ዘርዝሩ መጽሐፍ ውስጥ ማግኘት ካልተቻለ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት ቢቻል ተቀራራቢ የሆነውን የሥራ ዓይነት ኮድ መሙላት ያስፈልጋል:: አንዳንድ ጊዜ በመስክ የተሞላው የሥራ ዓይነት ግልፅና በቀላሉ የማይነበብ ለመረዳትም አስቸጋሪ የሆነ ሊያጋጥም ስለሚችል ኢዲተሩ በእርጋታና በትዕግስት መረጃ ከሰብሳቢው የሞላውን ማጣራት ይኖርበታል::

ከዚህም በተጨማሪ ከሥራ ዓይነት ኮድ ዝርዝሩ ጋር ለማገናኘት ሲሞክር በቅድሚያ የተጠቀሰው የሥራ ዓይነት በየትኛው ዋና ክፍል እንደሆነ መለየየት ከዚያም በዋና ክፍሉ ሥር ከተዘረዘሩት የሥራ ዓይነቶች ለየትኛው እንደሚቀርብ አመዛዝኖ ኮድ ማድረግ ያስፈልጋል:: በሆኑም ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በመጠራጠር ኮድ ከማድረግ በመቆጠብና ተቆጣጣሪውን በማማከር ትክክለኛውን ኮድ መስጠት ይገባል:: በኮድ ዝርዝሩ ከተሰጠው የማጣጣም ሆኖ ከተገኘ ከተቆጣጣሪውና ከአሰሪው ክፍል ጋር ተነጋግሮ አዲስ ኮድ መስጠት ሊያስፈልግ ይችላል::

ዓምድ 32:- <u>በዋነኛነት የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድን ነው?</u>

በተመሳሳይ ሁኔታ በጥናቱ ሳምንት በሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸው በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ላልነበሩ ግለሰቦች በዚህ ዓምድ በዋነኝነት የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት /ኢንዱስትሪ/ ተሞልቶ መጥቷል:: ለዚህ የኢንዱስትሪ ዓይነት ተገቢ የሆነው የመለያ ኮድ ከ" <u>የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ኮድ ዝርዝር</u>" ተብሎ የተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ይሞላል:: የኢንዱስትሪ ዓይነቱን ከኮድ ዝርዝሩ መጽሐፍ ውስጥ ማግኘት ካልተቻለ ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ቢቻል ተቀራራቢ የሆነውን የኢንዱስትሪ ዓይነት ኮድ መሙላት ያስፈልጋል:: በመስክ ላይ የተሞላው የድርጅት ምርት/አገልግሎት ሳይሆን የድርጅቱ ስም ወይም ሌላ መግለጫ ሊሆን ይችላል:: በዚህን ጊዜ ከተቆጣጣሪው ጋር በመመካከር የድርጅቱ ዋና ምርት/አገልግሎት ምን እንደሆነ ለማወቅ የተለያዩ ግንዛቤዎችን ሁኔታዎችን በመውሰድ ለመሙላት ይሞከራል::

ዓምድ 33:- <u>የዋነኛ ሥራዎ የቅጥር ሁኔታ ምንድን ነው?</u>

ለዓምዱ የተሰጠው ክፍት ቦታ ተሞልቶ የመጣው የቅጥር ሁኔታ ከሥር በካርድ ኮለሙ ከተሞላው ኮድ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም ጥያቄው ሥር የተዘረዘሩት 11 አማራጭ መልሶች ከኮድ 01-11 ብቻ ስለሆኑ ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ ሳይሞላ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: እንዲሁም ከኮድ 06-09 የተሞላላቸው ግለሰቦች ተከታዮቹን ዓምዶች ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 39 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ሲገባ ኮድ 10 የተሞላላቸው ደግሞ ወደ ዓምድ 40 መሸጋገራቸውን ማጣራት ተገቢ

ይሆናል:: የአማራጭ መልሶች ዝርዝር መጠይቁ ላይ ከጥያቄው ሥር ቀርበዋል::

ዓምድ 34:- <u>ለሥራዎ የሚከፈልዎት በገንዘብ ነው ወይስ በዓይነት?</u>

በዚህ ዓምድ ጥያቄው የተጠየቀላቸው ከላይ /06-10/ በዓምድ 33 ከኮድ 01-05 እንዲሁም ኮድ 11 ለተሞላላቸው ስለሆነ ከነዚህ ኮዶች ውጭ (06-10) የተሞላላቸው ግን ይህንን ዓምድ አለመጠየቃቸውንና ከተጠየቁም በጥንቃቄ ታርሞ ተገቢወ ኮድ እንዲሞላላቸው ማድረግ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም ለዚህ ጥያቄ ለተሰጡት 3 አማራጭ መልሶች የተዘጋጁት 3 ኮዶች በመሆናቸው ከነዚህ ውጭ በተከታታይነት ተሞልተወ ከመጠት ሌሎች መረጃዎች ጋር በማገናዘብ ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ማስተካከል ተገቢ ይሆናል:: አማራጭ መልሶቹ ከጥያቄው ስር ስለተዘረዘሩ የተሞላውን ኮድ ተመሳሳይነትም ማገናዘብ ይገባል::

ዓምድ 35:- <u>ለዋናው ሥራዎ የአከፋፈል ጊዜ እንዴት ነው?</u>

ይህ ጥያቄ ግለሰቦች በዓምድ 33 ከኮድ 01-05 እንዲሁም ኮድ 11 ተሞልቶላቸው ከሆነ ብቻ የሚጠየቁት ስለሆነ እነዚህ ግለሰቦች ብቻ መጠየቃቸው መረጋገጥ ይኖርበታል:: ለዚህ ጥያቄ ለተሰጡት ሰባት አማራጭ መልሶች ከ1-7 ኮድ ተሰጥቶአቸው ከጥያቄው ስር ተዘርዝረዋል:: ስለሆነም፣ በዓምድ ስር በጽሁፍ የተገለፀው የአከፋፈል ጊዜና በካርድ ኮለሙ የተሞላው ኮድ መጣጣማቸው ይረጋገጣል:: በመጨረሻም ከኮድ 5-7 የተሞላላቸው ቀጣዩን /ሁለት ጥያቄዎች ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 38 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል::

<u>ዓምድ 36</u>:- <u>በገለፁልኝ አከፋፈል መሠረት ባለፈው ወር ለስንት የአከፋፈል ጊዜያት ሠርተዋል?</u>

በዚህ ጥያቄ ግለሰቦች በዓምድ 33 ከኮድ 01-05 እንዲሁም ኮድ 11 የተሞላላቸው ብቻ መጠየቃቸው ይረጋገጣል:: ጥያቄው በዓምድ 35 በተገለፀው የአከፋፈል ጊዜ መሠረት ለምን ያህል ጊዜ እየተከፈላቸው መሥራታቸውን ተጠይቀው ተሞልቷል በዚህ መሠረት ( ** 1)

በዓምዱ ሦስት ካርድ ኮለም የተሰጠ ቢሆንም በዓምዱ ከ"30" በላይ ሊገፍ የሚችለው በዓምድ 35 ኮድ "1" በየሰዓቱ የሚል የተሞላ ከሆነ ብቻ ነው:: ይህ ማለት ደግሞ "በየቀኑ" ኮድ "2" በዓምድ 34 ለተሞላለት ሰው 30 በየሰዓቱ ኮድ "1" ለተሞላት ደግሞ ከ100 በላይ ሊገፍ ስለሚችል ነው::

በየሳምንቱ ላለ ደግሞ ከ"4" መብለጥ አይኖርበትም:: ባጠቃላይ በዚህ ዓምድ ሊታይ የሚችለው ከፍተኛ ቁጥር "360" ነው::

<u>ዓምድ 37:-</u> <u>በገለፁልን አከፋፈል ለመሠረት ለመጨረሻ ጊዜ ምን ያህል ተከፈልዎት?</u>

ይህ ጥያቄ ገለሰቦች በዓምድ 35 ለገለፁት የአከፋፈል ሁኔታ በመጨረሻው ክፍያቸው ያገኙት የብር መጠን ተሞልቶ መጥቷል:: ለዚህም አራት ካርድ ኮለሞች የተዘጋጁ ስለሆነ በዚሁ መዓፊያ በተዘጋጁት ኮለሞች ቁጥሮች ከቀኝ ወደ ግራ መሞላቱን ማረጋገጥ ወሳኝ ነው:: ይህም ማለት የብሩ መጠን በካርድ ኮለሙ ሲፃፍ መጀመር የሚኖርበት ከቀኝ ይሆናል:: ስለዚህ "30 ብር" ያለ መልስ ሰጪ ብሩ በዓምዱ ሲሰፍር "0" "0" "3" "0" መሆን ይኖርበታል:: እዚህ ላይ ከብር "9997" እና በላይ ለሚከፈላቸው "9997" ብቻ መሞላት ይኖርበታል:: በተጨማሪም በደመወዝ ተቀጥረው ነገር ግን እስካሁን ክፍያ ያላገኙ ኮድ "9998" ተሞልቶ ከመጣ ኮድ እንጂ ብር እንዳልሆነ ታውቆ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 38:-</u> <u>በዋነኛነት ለሠሩት ሥራ ባለፈው አንድ ወር ወስጥ በጠቅላላው ምን ያህል ተከፈልዎት? ይህ ጥያቄ የመልስ ሰጪዎቹ አማካኝ ከሥራ የተገኘ የወር ገቢ መጠን</u>

የተጠየቀበት ሲሆን በዓምድ 38 ከተሞላው ጋር መነፃፀር አይኖርበትም:: ነገር ግን በተመሳሳይ መልኩም በካርድ ኮለሙ ውስጥ የቁጥሮቹ አፃፃፍ ከላይ በተገለፀው መሠረት ከቀኝ በመጀመር ይሆናል:: የወር ገቢያቸው ከብር "9997" እና በላይ ለሆነ የሚፃፈው ይኸው "9997" ይሆናል:: በሌላ በኩል ደግሞ እስካሁን ላልተከፈላቸው ኮድ "9998" የተሞላ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 39:-</u> <u>ድርጅቱ/የሥራ መልኩ ከ10 እና በላይ ሠራተኞች አሉት ወይም ? የሂሳብ መዝገብ አለው? ወይም ፈቃድ አለው?</u>

መልስ ሰጪዎች ስለሚሰሩበት ድርጅት የሂሳብ መዝገብ/የፈቃድ ሁኔታ ከ10 በላይ የሆነ ተቀጥሮ የሚሰሩ ሠራተኞች እንዳለውና እንደሌለው ተጠይቀዋል::

ለዚህም ጥያቄ ኮድ 1-3 ብቻ የተሰጠ ሲሆን፣ ከነዚህ ኮዶች ውጭ ሌላ አለመሞላቱ መረጋገጥ ይኖርበታል:: በዚህ ጥያቄ በዓምድ 33 ከኮድ 06-09 የተሞላላቸው ግለሰቦች መጠየቃቸው መረጋገጥ ይኖርበታል::

ዓምድ 40:- <u>አብዛኛውን ጊዜ በሳምንት ለስንት ሰዓት ይሠራሉ?</u>

በዚህ ጥያቄ ግለሰቦች አብዛኛውን ጊዜ በአማካኝ በሳምንት ውስጥ የሚሰሩት የስራ ሰዓት ተጠይቆ ተሞልቷል:: ስለሆነም አንድ ሰው ሊሞላለት የሚችለው ከፍተኛ የሳምንት የሥራ ሰዓት ብዛት 97 ነው:: ስለሆነም ከዚህ ቁጥር በላይ በካርድ ኮለሙ መታየት አይኖርበትም:: በተጨማሪ በዓምድ 33 ኮድ 10 የተሞላላቸው የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር አባላት መጠየቃቸው ይረጋገጣል::

ዓምድ 41:- <u>ሥራ ላይ ለነበሩ ባለፈው ሳምንት ተጨማሪ ሰዓት ለመሥራት አቅሙም ፍላጐትም ነበረዎ?</u>

ይህንን ጥያቄ በዓምድ 30 ኮድ 4 ከተሞላላቸው በስተቀር ሁሉም ይጠየቅላቸዋል:: ስለዚህ ይህ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል :: በተጨማሪም ለጥያቄው የተሰጡት አማራጭ መልሶች አዎን ኮድ 1 እና የለም፣ ኮድ 2 ስለሆኑ ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ ሌላ አለመሞላቱ መታየት አለበት:: በተመሳሳይ መልኩም ኮድ 1 የተሞላላቸው ቀጣዩን ጥያቄ ሲጠየቁ ኮድ 2 የተሞላላቸው ከሆነ ግን ከዚህ በኋላ ምንም ዓይነት ጥያቄ ሳይጠየቁ መረጃ መሙላት ማብቃት ይኖርበታል::

ዓምድ 42: <u>ተጨማሪውን ሰዓት በምን ዓይነት ሥራ ለመሰማራት ይፈልጉ ነበር?</u>

በዓምድ 41 አዎን ብለው ኮድ 1 የተሞላላቸው መልስ ሰጪዎች ለዚህም ዓምድ ይህንንም ጥያቄ ተጠይቀዋል:: በዓምዱ ደግሞ የተሰጡት አማራጮች ሦስት ስለሆኑ ለመረጃ ሰብሳቢው ከኮድ 1-3 ብቻ ኮድ መሙላቱን ማየት ተገቢ ነው:: ዝርዝር አማራጭ መልሶቹ ከጥያቄው ስር ስለተገለፁ ከተሞላው ኮድ ጋር መገናዘብ ይኖርበታል:: በመጨረሻም ይህንን ዓምድ የተጠየቁ መልስ ሰጪዎች በሙሉ የሚቀጥለው ክፍል ስለማይመለከታቸው የመረጃ መሙላቱ ተግባር ማብቃቱ ይረጋገጣል::

## ክፍል 5

## <u>ሥራ አጥና የሥራ አጥ ባህሪያት</u>

## / ከዓምድ 43-52 ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ/

በዚህ ክፍል መረጃ የሚሰበሰብላቸው ግለሰቦች ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ሥራ ላልሰሩና ሠርተውም በዓምድ 29 ላይ ከ4 ሰዓት በታች ለተመዘገበላቸው ነው:: ይህ ማለትም በዓምድ 30 ላይ የለም ብለው ኮድ 4 የተሞላላቸውን በሙሉ የሚመለከት መሆኑን በቅድሚያ መረዳቱ ተገቢ ይሆናል::

ዓምድ 43:- ባለፉት 3 ወራት ሥራ ለማግኘት ወይም የግል ሥራ ለመጀመር ጥረት አድርገው ነበርን?

በዚህ ዓምድ የሚጠየቁ ግለሰቦች በዓምድ 30 ላይ ኮድ 4 የተሞላላቸውና ከዓምድ 31 ጀምሮም እስከዚህ ዓምድ ድረስ በ----ሰረዝ የታለፈላቸው መሆኑን ማየትም ያስፈልጋል:: በዓምዱ የቀረቡት አማራጮች "አዎን" ብለው ለመለሱ ኮድ 1 እና "የለም" ላሉ ኮድ 2 ስለሆኑ በተገቢው ካርድ ኮለም ከሁለቱም ኮዶች አንደኛው ብቻ መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባል:: ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 45 መሻጋራቸውን ማየት ያስፈልጋል::

ዓምድ 44:- ሥራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ምን ጥረት አደረጉ?

ግለሰቦች የራሳቸውን ወይም በቀጥር ሥራ ለመጀመር ከሚያደርጉት ሙከራዎች ውስጥ ስምንት አማራጮች ተቀምጠዋል:: ለዚህም በዓምድ 43 ኮድ 1 የተሞላላቸውን ብቻ ይመለከታል:: ስለሆነም እነዚህ ግለሰቦች ብቻ እንደተጠየቀላቸውና በቋበሮቁ ግርጌ ከተሰጡት 8 አማራጭ መልሶች አንዱንና ከኮድ 1-8 ብቻ በካርድ ኮለሙ መሞላቱን ማጣራት ይኖርበታል:: ከዚያም ይህንን ጥያቄ የመለሱ በሙሉ ቀጣዩን ዓምድ አለመጠየቃቸውንና ወደ ዓምድ 46 መሻገራቸውን ማጣራት ያስፈልጋል::

ዓምድ 45:- ለምንድን ነው ሥራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ጥረት ያላደረጉት?

በመጀመሪያ ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው በዓምድ 43 "የለም" ብለው መልሰው ኮድ 2 ለተሞላላቸው ማለትም ሥራ ለማግኘትም ሆነ መጣል ለመጀመር ምንም ጥረት ላላደረጉ ግለሰቦች ብቻ ነው:: ሥራ ለመሥራት ወይም ለማግኘ ት ጥረት ያላደረጉበት ምክንያት በዓምዱ ግርጌ ከተዘረዘሩት 12 አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ በዓምዱ ሥር መሞላቱንና ተገቢው ኮድ ደግሞ በካርድ ኮለሞቹ መሞላቱን ማረጋገጥ ያሻል:: የተሰጡት ኮዶች ከ01-12 ካልሆኑ በካርድ ኮለሞቹ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮችም ከነዚህ ውጭ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

ዓምድ 46:- በሚቀጥለው አንድ ወር ውስጥ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ቢያገኙ ይሠራሉ?

ለዚህ ጥያቄ "አዎን" የመለሱ ግለሰቦች ኮድ 1 "የለም" ብለው ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 እንደተሞላላቸውና በካርድ ኮለሙ ውስጥ መታየት የሚገባቸው ቁጥሮችም ከነዚህ ውጭ እንዳልሆኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በሌላ በኩል ደግሞ "የለም" ብለው ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 47 መሻገራቸውን ማጣራት ተገቢ ነው:: በዓምድ 44 የተጠየቁት ሁሉ ይህንን ጥያቄ መጠየቃቸውን ይረጋገጣል::

ዓምድ 47: በአቅምዎ ተቀጥረው ሊሰሩት የሚችሉት ሥራ ቢገኝልዎት ወይም በግል ሥራ ለመሠማራት አስፈላጊ ነገሮች ቢሟሉ ሥራ ለመጀመር ዝግጁ ነዎት ?

በዚህ ዓምድ የሚጠየቁት ግለሰቦች በዓምድ 46 ላይ "አዎን" ብለው መልሰው በሚቀጥሉት 1 ወር ሥራ ቢያገኙ ለመስራት ዝግጁ የነበሩትን /ኮድ 1 የተሞላላቸው/ ሲሆኑ ለዚህ ጥያቄ ዝግጁ መሆንና አለመሆናቸው ተጠይቀው ከተሰጡት 2 አማራጮች አንዱ ብቻ መሞላቱን ይረጋገጣል:: ዝግጁ ሆነው ኮድ 2 የተሞላላቸው ደግሞ ቀጣዩን ጥያቄ ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 49 መሸጋገራቸውን ማጣራት ተገቢ ነው

ዓምድ 48:- ለምንድነው ሥራ ቢያገኙ የማይሠሩት?

ይህ ጥያቄ የሚመለከታቸው ዝግጁ እንዳልነበሩ የገለፁ/በዓምድ 47 ኮድ 1 የተሞላላቸውን/ ነው:: ስለሆነም በዚህ ጥያቄ ከተዘረዘሩት ስምንት አማራጭ መልሶች መካከል አንዱን ብቻ መምረጣቸውንና ከኮድ 1-8 ብቻ በካርድ ኮለሙ መፃፉን ማጣራት ያሻል:: በተጨማሪም ይህንን ጥያቄ የተጠየቁ በሙሉ የቀሩትን ጥያቄዎች መጠየቅ የለባቸወም::

ዓምድ 49:- የሚፈልጉት ሥራ ምን ዓይነት ነው?

በዓምድ 47 "ዝግጁ ነኝ" ብለው ኮድ 2 የተሞላላቸው ግለሰቦች በዚህ ጥያቄ ደግሞ ምን ዓይነት ሥራ ለመሥራት እንደሚፈልጉ ተጠይቀዋል:: ለጥያቄው የተሰጡት አምስት አማራጮች ከጥያቄው ስር ተዘርዝረዋል:: ከነዚህ አማራጮች ውስጥ ከኮድ 1-3 የተሞላላቸው ብቻ ቀጣዩን ጥያቄ/ዓምድ ተጠይቀዋል:: ስለሆነም ከኮድ 4-5 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 51 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

ዓምድ 50:- የግል ሥራ/የራስን ድርጅት ለማቋቋም የገጠሞት/ የሚገጥምዎት ችግር አለ ? ካለ ምንድን ነው?

ለዚህ ጥያቄ የተሰጡት ዘጠኝ አማራጭ መልሶች ከመጠይቁ ግርጌ የተዘረዘሩት ናቸው:: እነዚህም አማራጮች በዓምድ 49 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው ግለሰቦች ብቻ ይቀርብላቸዋል:: በዚህ ዓምድ በአብዛኛው የሚያጋጥመው ችግር በዓምድ 49 ላይ ኮድ 4 እና 5 የተሞላላቸውም ይህንን ጥያቄ ተጠይቀው በዚህ ዓምድ ላይ ኮድ 09 ሌላ በሚለው ስር ምክንያት ተሞልቶ ይመጣል:: ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት ስህተት ሲኖር መታረም ይኖርበታል::

ዓምድ 51:- ለምን ያህል ወራት ያለሥራ ቆይተዋል?

በዓምድ 49 የሚፈልጉትን ሥራ ምን ዓይነት እንደሆነ ተጠይቀው "ተቀጥሮ ለመሥራት" ኮድ 4 እንዲሁም ሌላ ብለው ለገለፁና ኮድ 5 የተሞላላቸው በሙሉ ይህንን ጥያቄ ይጠየቃሉ:: በዚህ ዓምድ ሁለት ካርድ ኮለሞች የተሰጡት ሲሆን፣ በክፍት ቦታዎቹም ከኮድ "00" ጀምሮ ተሞልቶ ሊመጣ ይችላል:: በተጨማሪም በአንድ አሀዝ ዲጅት/Digit/ ብቻ የተፃፉ ቁጥሮችን ከግራ በኩል ባለው ካርድ ኮለም ተጽፎ ከተገኘ በቀኝ በኩል ባለው መጨረሻ ካርድ ኮለም ተሞልቶ መታረም ይኖርበታል::

ዓምድ 52:- ከዚህ በፊት በቅጥር ወይም በግል ሥራ ሠርተው ያውቃሉ?

ለዚህ ጥያቄ "አዎን" ብለው የመለሱ ኮድ 1 "የለም" ብለው ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 ተሞልቶላቸዋል:: ስለሆነም ከሁለቱ አማራጮች ውጭ የተለየ ኮድ ቁጥር አለመሞላቱ ይረጋገጣል::